# ጥናት አንድ አሞጽ 1፡1-15 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. አሞጽ ትንቢቱን የተናገረበትን ትክክለኛውን ወቅት ለመጠቆም የተነገሩት ነገሮች፡ ዖዝያን የተባለው የይሁዳ ንጉስ በነገሰበት ወቅት እንደሆነ፣ የዮአስ ልጅ ኢዮርብአም ደግሞ የእስራኤል ንጉስ በነበረበት ጊዜ መሆኑንና፣ ሶስተኛው መረጃ ደግሞ፤ የምድር መናወጥ ከሆነበት ከሁለት ዓመት በፊት እንደነበረ ይነግረናል። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የእግዚአብሄርን መልዕክት ተቀብሎ ለሕዝቡ የሚያስተላልፈውን ሰው ስንመለከት የነብይነት ልምድም ሆነ ዝግጅት ያልነበረው በተቆሔ ከነበሩ እረኞች መሃል አንደኛው እንደሆነ በቁ1 ላይ እናነባለን።
2. እግዚአብሄር ምን ጊዜም ቢሆን፤ የራሱም ህዝብ ሆነ የአህዛብ መንግሥታት ላይ ሲፈርድ የሚታየው በአንድ ምክንያት እንደሆነ በተደጋጋሚ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እናገኛለን፤ ይኸ ለፍርድ ምክንያት የሚሆነው ነገር “ሐጥያት” የሚባለው ነው። ሁሉም ሃጥያት እንደሰሩና ስለሰሩትም ሃጥያት እንደሚፈረድባቸው ስንመለከት፤ የሃጥያታቸው ዓይነት ግን የተለያየ እንደሆነ እንመለከታለን፤ ደማስቆ ገለዓድን በባሄዷ፣ ጋዛ ደግሞ ሕዝብን ማርካ ለኤዶም በመሸጧ፣ ጢሮስ ቃል ኪዳን በማፍረሷና የመሳሰሉትን በመጥቀስ በተለያዩ የሓጥያት ዓይነቶች እንደሰለፉ ነው የምናየው።
3. እያንዳንዱን ሃገሮች ከጠራና ያደረጉትን ነገር ከዘረዘረ በኋላ ለዚህ ላደረጉት ሃጥያታቸው ሊፈርድባቸው ያለውን ነገር በመንገር እግዚአብሄር በፍጥረት ሁሉ ላይ ስለ ሃጥያት ለመፍረድ መብት ያለው እርሱ እንደሆነ ግልጽ በሆነ ዓይነት መንገድ ይናገራል። በሁሉም አገሮች ላይ ሊመጣ ያለውን የፍርድ ዓይነት ስንመለከት ለሁሉም የተነገረውና ተመሳሳይነት ያለው የጋራ የሆነው የተነገረው ሃሳብ “እሳት እሰዳለሁ” በማለት የሚናገረው ሃሳብ ነው።
4. “ስለ ሶስቱ … ሃጥያት፤ ይልቁንም ስለ አራቱ ቁጣዬን አልመልስም።” ብሎ ሲናገር እኔ የሚገባኝ እነዚህ ሃገሮች ሶስት ጊዜ ወይም አራት ጊዜ ብቻ ሃጥያት ሰርተዋል ማለቱ ሳይሆን፤ የሃጥያታቸውን ብዛትና ተደጋጋሚነት ለማጉላት የተጠቀመው የአነጋገር ዘይቤ እንደሆነ ነው እኔ የምረዳው። አገሮቹ ሁሉ የተለያዩ የሚከሰሱባቸው ሃጥያቶች እንዳሉ በሌሎቹ ቁጥሮች ውስጥ ማየት የሚቻል ሲሆን፤ በዚህ ክፍል ግን ጢሮስ የምትከሰስበት ነገር፤ የወንድማማችን ቃል ኪዳን በማፍረስ የሚል ነው።
5. ኤዶም በመባል አብዛኛውን ጊዜ በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ የምናገኘው ሰው በዘፍ 36፡1 ላይ ስንመለከት የያዕቆብ ወንድም የሆነው የይስሃቅ ልጅ ኤሳው እንደሆነ እናያለን። እግዚአብሄር ከኤዶም ይጠብቅ የነበረው ነገር እንደነበረ ግልጽ ሲሆን፤ ይህም ነገር ርህራሄን ለወንድሙ ለእስራኤል ማሳየት ነበረ። ይህ ሁለቱን ወንድማማቾች በማሳየት እግዚአብሄር ሊያስተምረን የፈለገው ነገር፤ እኛም ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ርህራሄና ምህረት በሚያስፈልጋቸው ጊዜ ለመስጠት ፈቃደኞች ባንሆን እግዚአብሄር ለዚያ ሃጢያታችን እንደሚፈርድብን ነው የምማረው።
6. አሞን የተባለው ሰው ወይም አሞናውያን በመባል የታወቁት ሰዎች አመጣጥ፤ ሎጥን እግዚአብሄር ከሰዶም እንዲወጣ ነግሮት ከወጣ በኋላ ሁለቱ ልጆቹ ለወደፊት አባታችን ከሞተ የሚተካ ዘር ያስፈልጋል በማለት አባታቸውን አስከረው ተራ በተራ ከአባታቸው ጋራ በመተኛት ከተወለዱት ልጆች መሃል ታናሺቱ የወለደችው ልጅ ነው አሞን ተብሎ የተጠራው። አሞን እንደዚህ የነፍሰ ጡር ሴቶችን ሆድ እስኪቀድ ድረስ ጭካኔ ውስጥ እንዲገባ ምክንያት የሆነውን ነገር ቁ13 ሲናገር የራሱን ድንበር ለማስፋት ከነበረው ፍላጎት የተነሳ መሆኑን ነው የምንመለከተው።
7. አሞጽ ከእግዚአብሄር ለሕዝቡ ለእስራኤል የሚሆነውን የተለየ መልዕክት እስከተቀበለበት ጊዜ ድረስ፤ በተቁሔ ከሚገኙት እረኞች ጓደኞቹ ጋራ እለት ከእለት ከብቶቹን በማስወጣትና በማስገባት ላይ የተሰማራ ሰው እንደነበረ ነው የምንመለከተው። አሞጽ ሕይወቱን ሁሉ ይሰራ የነበረውና የሚያውቀው ነገር የእረኛነት ሥራ በመሆኑ፤ ምናልባትም ነብይ የሚባለውን ሰው አይቶ እንኳን ላያውቅ እንደሚችል ይመስለኛል፤ ስለዚህም ምላሹ ሊሆን ይችል ነበረ ብዬ የማስበው፤ እንደ ሙሴ የመናገር ችሎታ የለኝም ማለት ይችል ነበረ፣ የነብይነት እውቀትና ትምህርትም የለኝም፣ ከብቶቼን ለማንም ትቼ መሄድ አልችልምና፣ የመሳሰሉትን ምክንያቶች መደርደር ይችል ነበረ እላለሁ።

# <u>ጥናት ሁለት አሞጽ 2፡1-16 (ለመሪው የተዘጋጀ)</u>

1. እግዚአብሄር ስናጠፋ እየጠበቀ ለጥፋታችን ፍርድን ለመስጠትና ለመቅጣት ተዘጋጅቶ እንደተቀመጠ አድርገው የሚያስቡ ሰዎች አይጠፉም፤ ሆኖም በእነዚህ በምናየው በተለይም በኤዶም ላይ የሆነው ነገር ለእኔ የሚያስተምረኝ ነገር ቢኖር፤ እግዚአብሄር በሰዎች ላይ ግፍ ስናደርግና ሌሎችን በጭካኔ ስናስተናግዳቸው በእኛ ላይ ፍርዱን እንደሚያመጣ ሁሉ፤ ሌሎች ደግሞ በእኛ ላይ የሚፈጽሙትን በደልና ጭካኔ ስለሚመለከት የሚፈርድብን ብቻ ሳይሆን የሚፈርድልንም እንደሆነ ከኤዶም ተምሬአለሁ። በተጨማሪም እግዚአብሄር በቅዱሳን መሃል ብቻ ሳይሆን በአህዛብም መሃል ቢሆን በጽድቅ የሚፈርድ አምላክ እንደሆነም ማየት ችያለሁ።
2. ይህንን ቁጥር ስናነብ ይሁዳ የጎረቤት ሃገሮች የሚፈጽሙትን ያህል ሃጥያት በብዛትና በተደጋጋሚ ትለማመድ እንደነበረ የምናውቀው፤ እግዚአብሄር ለሌሎቹ የአህዛብ መንግሥታት ሁሉ እንደተነገረላቸው አይነት አነጋገርን ሲናገር ነው ቁ4 ላይ የምንመለከተው። ከይሁዳ ሃጥያቶች መሃል በዚህ ቁጥር ላይ ተዘርዝረው የምናገኛቸው ሶስት ነገሮች የሚከተሉት ናቸው፦ የእግዚአብሄርን ሕግ መናቅ፣ የእግዚአብሄርን ትዕዛዝ አለመጠበቅ፣ አባቶቻቸው በተከተሏቸው አማልክት፣ በሐሰት አማልክት በመመራት መሳሳታቸው ናቸው።
3. እግዚአብሄር ኢየሩሳሌም ለይሁዳ እንደ ምሽግ አድርጎ የተናገረላት ይህች ከተማ መቃጠሏ ትልቅ ነገር ሆኖ የሚታይበት ምክንያት፤ የእግዚአብሄር ቤተ መቅደስ እንዲሁም በኤር 52፡13 መሰረት የንጉስ ቤተመንግሥትም ስለነበረባት የሁሉ ነገር ማዕከል ነበረች፤ ምናልባትም ደግሞ ቤተ መቅደሱን እንደ እውነተኛ የአምልኮ ቦታ ሳይሆን ለግብር ይውጣ ብቻ ሥርዓት የመፈጸሚያ ቦታ አድርገውት ሊሆን ይችላል። እግዚአብሄር የተናገረው የፍርድ ቃል ፍጻሜ ለማግኘት ሁለት መቶ ዓመታት መውሰዱ ለእኔ የሚያስተምረኝ ነገር ቢኖር፤ እግዚአብሄር ክፉም ሆነ መልካም የተናገረው ነገር ቢዘገይም እንኳን ጊዜውን ጠብቆ መፈጸሙ እንደማይቀር ነው።
4. በመጀመሪያ ደረጃ የተጠቀሱት ሰዎች "ጻድቅ" የተባሉት ሲሆኑ፤ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ስለ ጥንድ ጫማ ብለው የሚሸጡት "ችግረኛ" ተብሎ የተጠራው ሰው፤ ሌላው ደግሞ በቁ7 በትቢያ ላይ ራሳቸውን የሚረግጧቸው "ድሆች" የተባሉት ሲሆኑ፤ በመጨረሻ ደግሞ ፍትህ የሚነጠቁት "ጭቁኖች" ብሎ በቁ7 ላይ የሚጠራቸው ናቸው። በእነዚህ ምስኪኖች ላይ እያደረጓቸው ያሉት ድርጊቶቻቸው በሙሉ በእግዚአብሄር በራሱ ላይ እንደተደረገ አድርጎ "እንዲህ እያደረጉ ቅዱስ ስሜን ያረክሳሉ" በማለት እየተበደለ ያለው እግዚአብሄር ራሱ እንደሆነ አድርጎ ሲናገር እንመለከተዋለን።
5. በመሰዊያው አጠገብ ወይም በአምላካቸው ቤት ውስጥ እየተጠቀሙባቸው ያሉት ነገሮች መገኛቸውን ቁ8 ሲነግረን፤ በመያዣነት የተያዙ ልብሶች እንደሆኑና፣ የሚጠጡት የወይን ጠጅ እንኳን በመቀጫነት የተወሰደ የወይን ጠጅ እንደሆነ እናነባለን። ሰዎች ዛሬም ቢሆን በዘመናችን በግፍ፣ በስርቆት፣ በማጭበርበርና፣ በተለያዩ መንገዶች ያከማቹትን ገንዘብና ንብረት ለእግዚአብሄር ቤት እንደሚጠቅም ነገር አድርገው የሚያመጡ ሰዎች እንደማይጠፉ ምንም ዓይነት ጥርጥር የለኝም።
6. በተለይም ቁ9 ላይ ስናነብ የእስራኤልን ጠላት እግዚአብሄር የሚስለው፤ "ቁመቱ እንደ ዝግባ፣ ጥንካሬውም እንደ ባሉጥ ዛፍ የነበረ ቢሆንም" በማለት የተቃዋሚዎቻቸውን ሃይለኛነትና አስፈሪነት በዛፍ በመመስል ነው ሲናገር የምንመለከተው። በቁ11 ላይ ስናነብ እግዚአብሄር አምላካቸው ለህዝቡ ለእሥራኤል ጠላቶቻቸውን ከማጥፋት ባሻገር ያደረገላቸውን ነገሮች ሲዘረዝር፤ ከወንድ ልጆቻቸው መሃል ነብያትን እንዳስነሳላቸው፣ ከጎልማሶቻቸው መሃል ደግሞ ናዝራዊናንን እንዳስነሳላቸው ይነግራቸዋል።
7. እንደሚታወቀው ናዝራዊ የሆነ ሰው የሚያሰክር መጠጥ መጠጣት እንደሌለበት ከዘሑ 6፡4 እና ከተለያዩ ክፍሎች እንረዳለን፤ የእስራኤል ሰዎች ግን እነዚህን ናዝራዊያኑን እግዚአብሄር የከለከለውን የወይን ጠጅ እንዳጠጧቸው፤ ከእግዚአብሄር ዘንድ መልዕክት እንዲያመጡላቸው የተሰጧቸውን ነብያቱን ደግሞ ትንቢት እንዳይናገሩ እንዳዘዟቸው ነው የምናነበው።
8. እግዚአብሄር የእስራኤል ጠላቶች የመታበት መንገድ ከባድና የማያዳግም እንደነበረ የሚያረጋግጥልን ነገር በቁ9 ላይ የተነገረው አነጋገር ነው ይኸውም፤ የዛፉን ፍሬ አራግፎ ያቆመ ቢሆን፣ ወይም ደግሞ ፍሬ ያዘለውን ቅርንጫፍ ብቻ በመቁረጥ ያበቃ ቢሆን ኖሮ ተመልሶ ለማቆጥቆጥና ለሕዝቡ ቋሚ የሆነ ተግል ሊሆን እንደሚችል ስላወቀ የዛፉን ከታች ከሥሩ በመንቀል እንዳጠፉ የሚናገረው አነጋገር የማያዳግም ዓይነት እርምጃ እንደወሰደበት ነው ግልጽ የሚያደርግልን።

# ጥናት ሶስት አሞጽ 3:1-15 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. እግዚአብሄር የሕዝቡን የእስራኤልን መነሻና መሰረታቸውን እንዳይረሱና እንዳይዘነጉ ለማድረግ ምናልባትም እስከሚሰለቻቸው ድረስ በመደጋገም የተናገራቸው ሲሆን፤ አሁንም በዚህ ክፍል ውስጥ ይህንን ሲያደርግ የምናየው በቁ1 ላይ ከግብጽ ምድር ያወጣቸው ሕዝቦቹ እንደሆኑ ሲጠቁማቸው ነው የምንመለከተው። እስራኤል ከእግዚአብሄር የተቀበለችው በረከት ምን እንደሆነ ቁ2 ላይ "ከምድር ወገን ሁሉ አንተን ብቻ መረጥሁ" የሚለው አነጋገር ለዚህ ሕዝብ ምን ያህል እንደገባቸው አላውቅም፤ ሆኖም እስራኤል ብቻ ሳትሆን እኛ ራሳችንም በክርስቶስ ያገኘናቸውን በረከቶች ሁሉ ምን ያህል የከበሩ እንደሆኑ ለመረዳት ስንቸገር እመለከታለሁ።
2. ነብዩ አሞጽ "በውኑ ሁለት ሰዎች ሳይስማሙ አብረው መጓዝ ይችላሉን?" በማለት የሚናገረው በዚህ አውድ መሰረት እግዚአብሄርና እስራኤል እንደሆኑ ነው የምረዳው፤ ምክንያቱም የወደዳትና ከምድር ወገን ሁሉ ለይቶ የጠራት ስትሆን ዛሬ ግን በሐጥያት ራሷን ከእርሱ ስለለየች እግዚአብሄር ከሐጥያት ጋራ መተባበር ስለማይችል ሁኔታው መስተካከል ይኖርበታል ማለት ነው። ይህንን ክፍል ስረዳው፤ እግዚአብሄር ከእስራኤል ጋራ አብሮ ለመሄድ እንደማይችል የተናገረው ሃጥያት በመሃል ስላለና ያ ሃጥያት ከመሃል ሊወገድ ያስፈልጋል ማለቱ እንጂ በቃ ከአሁን በኋላ እግዚአብሄርና እስራኤል አብረው መሄድ አይችሉም ማለቱ አይደለም።
3. የመጀመሪያው ምሳሌ አንበሳ የሚበላውን ነገር ሳያገኝ በጫካ ውስጥ እንደማይጮህ፣ የሚቀጥለውና ሁለተኛው ምሳሌ ደግሞ ወጥመድ ሳይዘረጋ ወፍን ለማጥመድ እንደማይሞከር የሚገልጽ ሲሆን፤ ሶስተኛው ምሳሌ ደግሞ የመለከት ድምጽ በከተማ ውስጥ በተሰማ ጊዜ የህዝቡ ልብ እንደሚደነግጥ የሚናገር ነው። እነዚህ ሶስቱ ምሳሌዎች እግዚአብሄር ከህዝቡ ጋራ በአሁኑ ወቅት ስላለው ግንኙነት ሊያሳዩን የሚችሉት ነገር፤ እነርሱ በሐጥያት ውስጥ እንዳሉና ፍርዱን ሊያመጣባቸው እንደሆነ በተለያየ መንገድ የተናገራቸውን ማስጠንቀቂያ ችላ እንዳይሉት፤ አንበሳ ሲያገሳ ምግብ እንዳገኘ፣ የሚይዘው ሳይኖር ወጥመድ እንደማይፈናጠርና፣ ጦርነት ሳይኖር መለከት እንደማይነፋ ሁሉ፤ እግዚአብሄርም ይህንን ሁሉ የሚናገረው ለጉራ እንዳልሆነ ማስጠንቀቁ ነው።
4. እነዚህ ሶስት ምሳሌዎች ብለን ያልናቸው ለእስራኤል በአሁኑ ሰዓት የመነገራቸው ዋነኛ ምክንያት አድርጌ የማየው፤ አምላካቸው እግዚአብሄር ምህረትን የሚወድ ስለሆነ ከሓጥያታቸው ንስሃ በመግባትና ወደ እርሱ በመመለስ ከአምላካቸው ጋራ እርቅን በማድረግ ከፍርድ እንዲድኑ ነው። በኖህ አማካኝነት ለዓለም ሕዝብ፣ በአብርሃምና በሎጥ አማካኝነት ለሰዶምና ገሞራ ህዝብ፣ በዮሴፍ አማካኝነት ለግብጽና በመሳሰሉት ባሪያዎቹ ምሥጢሩን እንዳስታወቀ፤ በዚህ ክፍልም ውስጥ ባሪያውን አሞጽን ተጠቅሞ በሃጥያታቸው ምክንያት ፍርድ ሊመጣባቸው እንደሆነ ገልጾላቸዋል።
5. እኔ እንደሚመስለኝ ከሆነ እስራኤል በእግዚአብሄር ሕግ ሲመዘን ብቻ ሳይሆን በአካባቢው የአህዛብ መንግሥታት ድርጊት ጋራ ሲመዛዘን እንኳን እንድርሱን የሚያስገርም ዓይነት ግፍ፣ ቅሚያና ንጥቂያና ዝርፊያ ሁሉ እየተካሄደ መሆኑን፣ ከአህዛብ የባሰ ሞራል ውስጥ እንደሚገኙ ሲያሳያቸው ይመስለኛል። እግዚአብሄር ይህንን ሲናገር እኔ የሚመስለኝ ሕዝቡ የእግዚአብሄርን በጎነት ለጎረቤቶቻቸው የሚናገሩ ብቻ ሳይሆን በጎነትን እርስ በእርስና ለአካባቢያቸው ሁሉ ማሳየት ከሕጉ የተማሩም እንኳን ቢሆን፤ ሕይወታቸው ከተሞላው ክፉት፣ ንጥቂያና ጨቆና ብዛት የተነሳ በጎ ማድረግ የሚለው አስተሳሰብ ከውስጣቸው እንደወጣ ለመጠቆም ነው።
6. በመጀመሪያ ደረጃ ጠላታቸው የሚያደርገው ነገር ምድሪቱን መውረር ነው፤ ሁለተኛው ጠላት የሚያደርገው ነገር ደግሞ የተማመኑበትና ቅሚና ዝርፊያን ያካሂዱበት የነበረውን ምሽጋቸውን ማፍረስ ሲሆን፤ በሶስተኛ ደረጃ የሚያደርገው ነገር ደግሞ ድንኳኖቻቸውን ወይም መኖሪያቸውን ይዘርፋል። በቁ14 ላይ እንደሚያፈርሳቸው የሚናገራቸው ሁለት ዓይነት ቤቶች፤ አንደኛው ለእነርሱ መዝናኛ ተብለው የተሰሩትን የበጋና የክረምት ቤቶች የሚያጠቃልል ሲሆን፤ ሌላኛው ደግሞ በእግዚአብሄር ፈቃድ ሳይሆን ነገር ግን በእነርሱ አስተሳሰብ ለእግዚአብሄር ተብሎ የተሰራውን የቤቴልን መሰዊያ እንደሚያፈርስ ነው።
7. እግዚአብሄር እስራኤልን ከምድር ነገዶች ሁሉ መሃል በመለየት የራሱ ሕዝብ አድርጎ እንደመረጣት ሲታወቅ፤ በዚህ በቁ2 ላይ ፍቅሩና ፍርዱን አንድ ላይ ስናይ የምንማረው ነገር ቢኖር፤ እግዚአብሄር ወደደን፣ ወይም ደግሞ ከሌሎች በተሻለ መንገድ በረከቱንና ስጦታውን በእኛ ላይ አትረፈረፈልን ማለት ከሃላፊነት ነጻ ሆነናል፤ እንደወደድን መኖር እንችላለን ማለት እንዳልሆነ፤ ነገር ግን ከእግዚአብሄር የምንቀበለው ማናቸውም ከሌሎች የበለጠ የሚመስል ነገር ሁሉ ከሃላፊነት ጋራ የሚመጣ መሆኑን ነው የሚያስተምረን።

# <u>ጥናት አራት አሞጽ 4፡1-13 (ለመሪው የተዘጋጀ)</u>

1. በነብዩ ውስጥ የሚተላለፈውን መልዕክት እንዲሰሙ የፈለገው፤ አንደኛው በሰማርያ ተራራ ላይ የሚኖሩ የባሳን ላሞች ሲሆኑ፣ ሌሎቹ ደግሞ ድሆችን የሚጨቁኑና ችግረኞችን የሚያስጨንቁ፤ እንዲሁም ባሎቻቸውን መጠጥ አቅርቡልን የሚሉትን የእስራኤል ሴቶች ነው የሚናገረው። ድሆችና ችግረኞች ራሳቸውን መከላከል ወይም ለራሳቸው የሚያስፈልጋቸውን ነገር ለማድረግ ምንም ዓይነት አቅም የሌላቸው ዓይነት ሰዎች በመሆናቸው እግዚአብሄር ሁልጊዜ ከእነርሱ ወገን እንደሚቆም ሲናገር እናገኘዋለን፤ ይህ ማለት ግን እግዚአብሄር ስንፍናን ያበረታታል ማለት እንዳልሆነ ጳውሎስ በተሰሎንቄ መልዕክት ላይ የተናገረውንና ሌሎችን ጥቅሶች ስናነብ ትክክለኛውን ሃሳብ እናገኛለን።
2. እነዚህ ፍርድ እየተነገረላቸው ያሉት ሰዎች ወደሚሄዱበት ሥፍራ እንዴትና በምን ሁኔታ እንደሚሄዱ ግልጽ የሚያደርግልን ቃል ሁለት ጊዜ የተጠቀሰ ሲሆን፤ ይህም ቃል "መንጠቆ" የሚለው ነው፤ ይህ የሚያሳየን አሳ በፈቃዱና ወዶ ከሚኖርበትና ከሚመቸው ውሃ ውስጥ የሚያወጣው መንጠቆው እንጂ ፈቃደኛነቱ እንዳልሆነ ሁሉ፤ ለእነዚህም ሰዎች በአፍንጫቸው የገባው መንጠቆ እንጂ ፈቃደኛነታቸው እንዳልሆነ ማየት ይቻላል። ማንም በእርግጠኛነት መናገር የሚችለው ነገር አይደለም፤ ሆኖም ምናልባት የንስሃ ጊዜ መስጠቱ ሊሆን እንደሚችል ነው እኔ የምገምተው።
3. የአምልኮ ቦታ ተብሎ በሚታሰበው በቤቴል ሃጥያት መስራታቸው፣ በጌልጌላም ሃጥያታቸውን ማብዛት እንዳፋፋሙት፣ በማለዳ መስዋዕታቸውን ያለማቋረጣቸው፣ በየሶስቱ ዓመት አስራት ማቅረባቸው፣ እርሾ ያለበትን እንጀራ መሥዋዕት አድርገው ማቅረባቸው፣ በፈቃዳቸው በሚያቀርቡት መስዋዕት መመካት የሚሉት ናቸው። ይህንን ሁሉ የሃይማኖት ሥርዓት እንደሚገባ ያከናውናሉ፤ ሆኖም ግን እግዚአብሄር የሚጸየፈውን ድሆችን ማስጨነቅና ድሆችን መጨቆን ደግሞ ልማዳቸው ማድረጋቸው ድርጊታቸው ግብዝነት የሞላበት መሆኑን ያስገነዝበናል።
4. እግዚአብሄር በድርጊታቸው እንዳልተማረከና ደስ እንዳልተሰኘ በተለያዩ መንገዶች የገለጽ ሲሆን፤ እስራኤላውያኑ ግን እያደረጉት ስላሉት ሃይማኖታዊ ሥርዓቶች በቁ5 ላይ እንደምናነበው ከሆነ የሚመኩበት ነገር እንደሆነና እንዲሁም ማድረግ የሚወዱትም ነገር እንደሆነ ጭምር እግዚአብሄር ሲከሳቸው ይታያል።
5. በዚህ ቁጥር ውስጥ የሆነው ድርጊት በእስራኤላውያን ዓይን እውነትም ይህንን ያደረገው እግዚአብሄር ራሱ ነው ሊያሰኛቸው የሚችለው እኔ የሚታየኝ ነገር፤ ልክ በግጻዊያን ከተሞች ጨለማ፣ በእነርሱ ሰፈር ግን ብርሃን በማድረግ እንደለየ ሁሉ፤ በዚህም ክፍል በአንዱ እርሻ ላይ አዝንቦ አጠገቡ ባለው ያለው እርሻ ግን ዝናብ እንዳያገኝ ሆኖ እንዲደርቅ መደረጉ ሊያነቃቸው ይችል እንደነበረ አስባለሁ።
6. በዚህ ዓውደ ምንባብ ውስጥ ስንመለከት የእግዚአብሄር ህዝብ አንገቱን አደንድኖና ከክፋቱ አልመለስ ብሎ ያስቸገረበት፤ በተለያየ መንገድም በመጠቀም ወደራሱ ለመመለስ ቢሞክር እንቢተኛነታቸውን ያጠነከሩበት ወቅት ስለነበረ በዚህ ቦታ አምላካቸውን እንዲገናኙ የተነገራቸው ለፍርድና ለቅጣት እንጂ መልካምን ነገር ለመካፈል እንዳልሆነ ማየት እንችላለን። ይህ እንዲገናኙት የተጋበዙት እግዚአብሄር በመጀመሪያ ደረጃ ተራሮችን የሚሰራ አምላክ ነው፤ ነፋሳትን የሚፈጥር አምላክ ነው፤ ሃሳቡን ለሰው የሚገልጥ ነው፤ ንጋትን ጨለማ የሚያደርግ አምላክ ነው፤ የምድርን ከፍታዎች የሚረግጥ አምላክ ነው፤ ስሙም የሰራዊት አምላክ እግዚአብሄር የሚባል ነው።
7. እግዚአብሄር ረሃብን፣ ዝናብን በመከልከል፣ መቅሰፍትን በመላክና ሌሎችም ብዙ በዚሁ በተመለከትነው ምዕራፍ ውስጥ ተዘርዝረው የምንመለከታቸውን ነገሮች ሁሉ በማድረግ የሕዝቡን የእስራኤልን ልብ ለመመለስ ብዙ ጥረት እንዳደረገ፤ ነገር ግን እነርሱ ወደ አምላካቸው ለመመለስ ምንም ዓይነት ፈቃደኛነትን እንዳላሳዩ በተደጋጋሚ "እናንተ ግን ወደ እኔ አልተመለሳችሁም" በማለት ጥረቱ ሁሉ ስላልተሳካ የነበረው አማራጭ የሚገባቸውን ፍርድ መስጠት ስለነበረ ያንኑ ለማድረግ ሲወስን እናገኘዋለን።

# <u>ጥናት አምስት አሞጽ 5፡1-27 (ለመሪው የተዘጋጀ)</u>

1. እስራኤል እንደወደቀችና ተመልሳ እንደማትነሳ ሲናገር፤ በንስሃ ተመልሳ ወደ አምላኳ ማየት እስካልጀመረች ድረስ ለእስራኤል ከውድቀቷ ለመነሳት ሌላ ተስፋ ሊኖራት እንደማይችል፤ ለእስራኤል አንዱና ብቸኛ የሆነው ከውድቀት የመነሻ መንገድ እግዚአብሄር እንደተናገረው እርሱን በመፈለግ ብቻ በሕይወት ሊኖሩ እንደሚችሉ ነው የሚያስጠነቅቃቸው። እስራኤል ምንም ዓይነት ብርቱ ወታደሮቿን ወደ ጦር ሜዳ ብትልክ እንኳን ውጤቱን ቁ3 ሲናገር ከዘመቱት መሃል ወደ ቤታቸው የሚመለሱት ወታደሮች ቁጥር አሥር ፐርሰንቱ ብቻ እንደሚሆኑ አስቀድሞ ይነግራቸዋል፤ ይህም ማለት እግዚአብሄር የሌለበትን ጦርነት ለማካሄድ መሞከር ኪሳራው እንደሚበዛ ሲያሳያቸው ነው።
2. እግዚአብሄር በእነዚህ ቁጥሮች ላይ ለሕዝቡ በሚሰጠው ምክር ላይ ስንመለከት፤ በሕይወት ለመኖር ከፈለጉ አንዱና ብቸኛው መንገድ ምን እንደሆነና ያም ደግሞ እርሱን በመፈለግ ብቻ በሕይወት መኖር እንደሚችሉ ይነግራቸዋል። በሕይወት መኖር ብሎ እግዚአብሄር ሲናገር እስትንፋሳቸው እንዳለ ተጠብቆ መቆየት ወይም አለመሞት ብቻ ማለት አይመስለኝም፤ ነገር ግን ሰላም የሞላበት የተደላደለና ያለፍርሃት፣ በደስታና በሃሴት የተሞላ ዓይነትን መለማመድ እንደሆነ ነው የሚገባኝ። እነዚህ ሰዎች በሕይወት የሚያኖር መስሏቸው የሚያደርጓቸው ነገሮች በቁ5 ላይ የምናነባቸው ለጣዖት አምልኮ ወደ ቤቴል፣ ወደ ጌልጌላና ወደ ቤርሳቤህ መሄድ ነበረ።
3. በተለይም በእነዚህ ሶስት ቁጥሮች ውስጥ ትኩረት ተስጥቷቸው ትንቢቱ ያተኮረባቸው ሁለቱ ዓይነት ሰዎች፡ የመጀመሪያዎቹ ፍትህን ወደ መራርነት የሚለውጡ ሰዎች ተብለው ሲጠሩ፤ ሁለተኛዎቹ ደግሞ ጽድቅን ወደ ምድር የሚጥሉ ሰዎች በመባል ተጠርተዋል። በቁ7 ላይ የምናያቸው ሰዎች በሕብረተሰቡ ውስጥ ትላልቅ ቦታ ያላቸው፣ ፍርድን ለመስጠትና፣ ለመንሳት፣ ለማጣመምም ጭምር የሚችሉ በመሆናቸው፤ በቁ9 ላይ እግዚአብሄር በብርቱዎችና በታላላቆች ላይ የሚፈርድ እንደሆነ፤ የተመሸገ ማለትም ይደረስበታል የማይባለውን መድረስና ማጥፋት እንደሚችል በመንገር እነዚህ ሰዎች የትም ማምለጥ እንደማይችሉ ለማስገንዘብ የተነገረ የማስጠንቀቂያ ሃሳብ እንደሆነ እገነዘባለሁ።
4. እነዚህ በእስራኤላውያን ሕብረተሰብ ዘንድ ተቀባይነት ያጡት ሁለት ዓይነት ሰዎች፤ የመጀመሪያዎቹ በፍርድ አደባባይ የሚገስጹ በማለት እንደነዚህ ዓይነት ሰዎችን እስራኤላውያኑ እንደሚጠሉ ሲናገር፤ ሁለተኛዎቹ ደግሞ እውነትን የሚናገሩ ሰዎች ሲሆኑ እነዚህም በእነርሱ ዘንድ የተናቁ እንደሆኑ ነብዩ ይነግረናል።
5. ሌሎች የሚፈጽሟቸው በደሎች፤ ድሆችን ይረግጣሉ፣ ድሃው እህል እንዲሰጣቸው ያስገድዳሉ፣ ጻድቁን ይጨቁናሉ፣ ጉቦን ይቀበላሉ፣ በፍርድ አደባባይ ከድሃው ፍትህ ይነጥቃሉ። እግዚአብሄር እንደገና ከእነርሱ ጋራ እንዲሆን ወይም ለዮሴፍ ቅሬታ እንዲራራ ከፈለጉ፡ አስተዋይ ሰው ዝም እንዲል፣ መልካሙን እንጂ ክፉውን እንዳይፈልጉ፣ ክፉውን እንዲጠሉ፣ መልካሙን ነገር ደግሞ እንዲወዱ፣ በመጨረሻም ደግሞ በፍርድ አደባባይ ፍትህን እንዳያጓድሉ ነው የተመከሩት።
6. እኛ አብዛኛውን ጊዜ የእግዚአብሄርን በጉባኤአችን መሃል እንዲያልፍ በጸሎትም ሆነ በዝማሬ ስንጠይቀው፤ ምህረቱን፣ ፍቁሩን፣ ቸርነቱንና ይቅርታውን ሁሉ ይዞ በመሃላችን እንዲመላለስ ሲሆን ልመናችን፤ በዚህ ክፍል ውስጥ በተለይም በቁ17 ላይ እግዚአብሄር አምላክ በመካከላችሁ አልፋለሁ ሲል ግን በምዕራፎቹ ውስጥ ሁሉ ሕዝቡ የሚያደርጉትና የሚሆኑትን በመመልከት ፍርድን ይዞ ድሃ አደጉንና ምስኪኖቹን ከጨቋኞች ለመታደግ የሚመጣበትን የበቀል አመጣጥ ነው የሚናገረው።
7. ዓመት በዓላቸውን ተጸይፎታል፣ ጠልቶታል፤ በጉባኤአቸው ደስ እንደማይሰኝ፤ የሚያቀርቡለትን የሚቃጠል መስዋዕትና የእህል ቁርባናቸው እንደማይቀበል፤ የሚያቀርቡለትንም የሕብረት መሥዋዕታቸውንም ዘወር ብሎ እንደማይመለከተው ሲናገር፤ ዝማሬአቸው ሁሉ ጩኸት እንደሆነበት፤ የበገና ዜማቸውም ሁሉ ከእርሱ እንዲያስወግዱት ነው የሚነግራቸው። በእርሱ ዘንድ ተቀባይነትን ማግኘት ከፈለጉ፤ እነዚህን ሁሉ ከሃይማኖታቸው የተነሳ የሚፈጽሟቸውን ሥርዓቶች አቁመው ሁለት መሰረታዊ ነገሮችን ብቻ እንዲያደርጉ በቁ24 ላይ ይመክራቸዋል፤ አንደኛው እንዲያደርጉ የታዘዙት ፍትህ በእነርሱ ዘንድ እንደ ወንዝ እንዲፈስ ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ጽድቅ እንደማይደርቅ ምንጭ እንዲፈስ ነው ትዕዛዙ።
8. በእኔ አመለካከት በዚህ በቁ10 ውስጥ የተነገረው ነገር በይበልጥ አሳፋሪ የሆነበት ምክንያት፤ እነርሱ ፍርድንና ጽድቅን እንዲያደርጉ፣ በእውነትም እንዲመላለሱ በተለያዩ ጊዜያት በእግዚአብሄር ትዕዛዝ የተቀበሉ ሲሆን፤ ነገር ግን ባለመታዘዝ እየኖሩ ከዚያ አልፈው ግን ሌሎች እግዚአብሄርን እየታዘዙ ለመኖር የሚሞክሩትን ሰዎችም በጥላቻና በንቀት በማስተናገድ ተስፋ ለማስቆረጥ መሞከራቸው ይበልጥ ሁኔታውን በእግዚአብሄርም ዘንድ ሆነ በሰዎች ፊት አሳፋሪና አስከፊ ያደርገዋል ብዬ አምናለሁ።

# ጥናት ስድስት አሞጽ 6፡1-7፡17 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. አንደኛው በጽዮን ተዘልለው የተቀመጡ ነው የሚላቸው፤ ሁለተኛው ደግሞ መለያቸው በሰማርያ ተራራ ላይ ያለሥጋት የምትቀመጡ ነው የሚላቸው፤ በሶስተኛ ደረጃ ደግሞ የእሥራኤል ሕዝብ ለእርዳታ ወደ እናንተ የሚመጡባችሁ ይላቸዋል። እነዚህ በዚህ ውስጥ በሶስት ዓይነት ነገሮች መለያ አድርጎ የተናገራቸውን ሰዎች ማንነት ሲነግረን ደግሞ አሞጽ "እናንተ የአህዛብ አለቆች ሆይ ወዮላችሁ" በማለት ማንነታቸውን ያጋልጣል። በቁ2 ውስጥ እነዚህ የአህዛብ አለቆች ራሳቸውን እንዲያስተያዩ የሚጋበዙት ከካልኔ፣ ከሃማትና፣ እና በመጨረሻም የፍልስጤም ከተማ ከሆነችው ከጌት ጋራ ነው።
2. በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የተዘረዘሩት ነገሮች በራሳቸው ሃጥያት ናቸው ማለት እንደማንችልና ለዚያም ምሳሌ ሊሆነን የሚችለው "ምርጥ ሽቱም ለምትቀቡ" የሚለውን ብንወስድ በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ ኢየሱስ ምርጥ የሆነ ሽቱ እንደተቀባ ስለምናውቅ የተከለከለ እንዳልሆነ መረዳት እንችላለን፤ ሆኖም እነዚህን ነገሮች ሁሉ በዓውዱ መሰረት ሃጥያት የሚያደርጋቸው ነገር በቁ6 ላይ ነብዩ የተናገረው ለዮሴፍ ማለትም ለህዝቡ የማያዝኑና ግድ የማይሰጣቸው፣ በራሳቸው ነገር ላይ ብቻ ያተኮሩ ጨካኞች መሆናቸው ነው።
3. ሕዝቡ በተለይም መሪዎችና አለቆች ተብለው የሚጠሩት በዚያን ወቅት በፈንጠዝያና በመዝናናት ላይ ይገኙ እንደነበረ፤ ቁ8ትን ደግሞ ስንመለከት የያዕቆብ ቤት በትዕቢት ተሞልቶ እንደነበረ ከዚህም የተነሳ ምሽግና ከለላ አድርጎ የሚመለከተው አምላኩን እግዚአብሄርን ሳይሆን ሌሎች ምሽጎች ለራሳቸው እንዳቆሙ እንመለከታለን። በዚህ ሥፍራ ላይ የማነጻጸሩን ሃሳብ በመጠቀም ለእነዚህ ሰዎች ሲናገራቸው የፈለገው ዋነኛው ሃሳብ በጭራሽ መደረግ የማይገባውን ነገር እንደሚያደርጉ፤ ማለትም ፍትህ ሰዎችን የሚፈውስ ነገር ሊኖን ሲገባው እነርሱ ግን ወደ መርዝነት እንደቀየሩት፤ ጽድቅ ደግሞ ጣፋጭ ነገር መሆን ሲኖርበት ወደ መራርነት የሚለውጡ ሰዎች መሆናቸውን ሲያመለክት ይነግራቸዋል።
4. መጽሐፍ ቅዱሳችን በተለያዩ ሥፍራዎች እንደሚያስተምረን እግዚአብሄር አምላክ ልጆቹ ጭንቀታቸውን በእርሱ ላይ ሊጥሉና ሊያርፉበት የሚችሉበት አምላክ እንደሆነ 1ኛ ጴጥሮስ ብቻ ሳይሆን ኢየሱስም ራሱ በማቴዎስ ውስጥ ሸክም የከበደባቸው ወደ እርሱ መጥተው ማረፍ እንደሚችሉ ሲናገር፤ ነብዩ አሞጽ ደግሞ የሚናገረው ሰው ከእግዚአብሄር ጋራ ተስማምቶ ለመኖር እንቢ ካለና በዓመጽ ለመኖር ሲወስን እግዚአብሄር ራሱ ለጭንቀቱ ምክንያትን ሊሆነው እንደሚችል ግልጽ አድርጎ ነው የሚናገረው።
5. እነዚህ እግዚአብሄር በእስራኤል ላይ ሊያመጣቸው የወሰናቸው ሁለቱ መቅሰፍቶች በአገሪቱ ላይ እንዳይመጡ የተከለከሉበት ምክንያት፤ በ7፡2 እና በ7፡5 ላይ እንደምናነበው ነብዩ አሞጽ በሕዝቡ ላይ ሊመጣ ያለው ነገር ስለከበደው ዝም ብሎ ሄዶ የተሰጠውን መልዕክት ከማስተላለፍ ይልቅ ከእግዚአብሄር ጋራ በመማጸን መቅሰፍቶቹ እንዲከለከሉ እንዳደረገ እናያለን። በዚህ ክፍል ውስጥ ከምናየው ከአሞጽ ድርጊት ለሕይወታችን መማር የምንችለው ነገር፤ እግዚአብሄር በሰዎች ላይ ሊያመጣ ያለውን ነገር አስታወቀን ማለት መልዕክቱን ከማስተላለፍ ሌላ ለሰዎች መራራትና፤ ስለሰዎች ደህንነት በእግዚአብሄር ፊት መማጸንም ጭምር እንደሚኖርብን ያስተምረናል።
6. የቤቴል ካህን በመባል ለሚታወቀው ለአሜስያስ ሴራና ክፋት ሆኖ የታየው የአሞጽ ትንቢት፤ ስለ ንጉሳቸው ስለ ኢዮርብዓም በሰይፍ መሞት፤ እንዲሁም እስራኤል ከትውልድ አገሩ ተማርኮ ወደ ምርኮ ምድር እንደሚሄድ የተናገረው ትንቢት ነው በእርሱ ዘንድ እንደ ሴራ ሆኖ የተወሰደው።
7. አሞጽ እረኛና የባሉጥ ፍሬ ለቃሚ እንደሆነ እንጂ እርሱ ራሱ ነብይ እንዳልሆነ ወይም ደግሞ በዘሩም እንኳን ነብይነት እንደሌለው ያስረዳዋል። አሞጽ ነብይ መሆንም ፈልጎ እግዚአብሄርን የጠየቀና ለነብይነት ፍላጎት ያሳየ ሰው እንዳልሆነ፤ ነገር ግን እግዚአብሄር ራሱ ሂድና ለህዝቤ ለእስራኤል ትንቢት ተናገር ተብሎ እንደታዘዘ፤ ስለዚህም እያደረገ ያለው ያንኑ እንደሆነ ይናገራል። መልዕክቱ ወደ ሕዝቡ እንዳይደርስ ይከላከል የነበረው ካህኑ አሜስያስ ይህንን በማድረጉ ሲደርስበት የምናየው ነገር፤ ቁ17 ላይ የሰፈረውን ለግሉ የሆነ አስፈሪ ትንቢት ወዲያው ሲመጣለት፤ ስለሚስቱ፣ ስለሴትና ወንዶች ልጆቹና ስለራሱም ጭምር የግል መከራ እንደሚያገኘው ነው የተነገረው።
8. የእግዚአብሔርን መልዕክት ለእግዚአብሄር ሕዝቦች ለማምጣት በሞከሩበት ወቅት በተለያዩ ዘመናት ብዙ ነብያት መናገር እንደተከለከሉ፣ እንደተደበደቡ፣ እንደተሰደቡና ብዙ ነገሮች እንደገጠሟቸው ከመጽሐፍ ቅዱሳችን መረዳት እንችላለን፤ ሆኖም በዚህ ክፍል ውስጥ የምንመለከተውን የነብዩን አሞጽ እንዳይተነብይ መከልከል አስገራሚ የሚያደርገው ነገር ቢኖር ትንቢቱን እንዳይናገር የከለከለው ሰው ካህን እንደነበረ ስናይ ሁኔታውን ትንሽ የተለይ ያደርገዋል እላለሁ።

# ጥናት ሰባት አሞጽ 8፡1-9፡15 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. የፍሬው መጎምራት ወይም መብሰል ከእስራኤል ሕይወት ጋራ በተገናኘ የሚያሳየው እውነት ቢኖር፤ የእስራኤል እንቢተኛነትና እግዚአብሄርን ለመስማት እንቢ ማለት ከጊዜ ወደ ጊዜ በዝቶ ልክ ፍሬ በስሎ ለመበላት ዝግጁ እንደሚሆን ሁሉ እስራኤልም ለፍርድ የተዘጋጀች እንደሆነች የሚያሳይ ምሳሌ ነው። በዚያን ቀን እግዚአብሄር የቤተ መቅደስን ዝማሬ ወደ ዋይታ ይለውጣል፤ እጅግ ብዙ የሆነ የሰው ሬሳ በመሬት ላይ ወድቆ ይገኛል፤ በምድሪቱም ላይ ዝምታ ይሰፍናል።
2. ነብዩ አሞጽ በአሞ 7፡4-6 ውስጥ የተለየ ትኩረት በመስጠት የሚያናግራቸው ሰዎች ቁ4 ላይ የምናገኛቸው፤ "እናንተ ችግረኞችን የምትረግጡና፤ የምድሪቱንም ድሆች የምታጠፉ ይህንን ስሙ" በማለት የሚናገራቸው ሰዎች ናቸው። እነዚህ ጨካኞችና ርህራሄን የማያውቁ ሰዎች የሚያደርሱባቸውን ሁኔታ ለመከላከል ድሆቹና ችግረኞቹ ምንም ዓይነት መከላከያ እንዳልነበራቸው ማየት ይቻላል። በዚህ ክፍል ውስጥ ለድሆቹና ለችግረኞቹ ቆሞ የሚሟገት ከሰዎች መሃል ማንም እንደሌለ፤ ነገር ግን ተሟጋች ሆኖ የምናገኘው ራሱ እግዚአብሄር አምላክ ነው። ኤር 22፡16 ሰዎች ለችግረኞችና ለድሆች መቆማቸው እግዚአብሄርን ደስ የሚያሰኝ ነገር እንደሆነ በግልጽ ያሳየናል።
3. ይህ ሊመጣ ያለው ቀን የምድር ሁለመና እንደ ዓባይ ወንዝ እንደሚነሳ፣ ፀሐይ በቀትር እንድትጠልቅ በማድረግ፤ ምድርን ደማቅ ብርሃን መሆን በሚገባው ሰዓት ጨለማ እንደሚያለብሳት፤ ዓመት በዓላቸውን ወደ ለቅሶ፣ ዝማሬአቸውንም ወደ ዋይታ እንደሚለውጠው፣ ሕዝቡ ሁሉ ማቅ እንዲለብሱ እንደሚያደርግ፣ ሁሉም ደግሞ ጠጉራቸውን እንዲላጩ በማድረግ ሁኔታውን አስከፊ ያደርግባቸዋል። ለአንድያ ልጅ እንደሚለቀስ የሚለውን አነጋገር፤ ሕዝቡን እስራኤልን ከፈርዖን እጅ ለማስለቀቅ በግብጻዊያን ላይ በመጨረሻ በማምጣት ግብጽን ሁሉ የለቅሶ ቦታ ያደረገውንና ሕዝቡን የታደገበትን ቀን ሊያስታውሳቸው ይችላል እላለሁ።
4. በነብዩ አሞጽ መልዕክት ውስጥ እግዚአብሄር ከእርሱ ሊሰወር ወይም ደግሞ ጠፍቶ ማምለጥ የሚቻልበት ምንም ዓይነት ሥፍራ ሊኖር እንደማይችል ግልጽ አድርጎ የተናገረ ሲሆን፤ መዝሙረኛው ዳዊትም እርሱ በራሱ የተረዳውን ከእግዚአብሄር መንፈስ የትም ሄዶ መደበቅ እንደማይቻል ተመሳሳይ የሆነ እውነትን ነው የምንማረው። "ለመልካም ሳይሆን ለክፉ፣ ዓይኔን በእነርሱ ላይ አደርጋለሁ።" የሚለው ሃሳብ፤ አካሄዳቸውንና አረማመዳቸውን ሁሉ ሊጠብቃቸውና ሊረዳቸው ሳይሆን ክፉን ሊያመጣባቸው፤ ከእነርሱ በተቃራኒ ወገን ሊቆምና ጠላት ሊሆናቸው ሁኔታቸውን ሁሉ በዘላለም ዓይኖቹ ይከታተላቸዋል ማለት ነው።
5. እግዚአብሄር አምላክ ሕዝቡን እስራኤልን ከግብጽ እንዳወጣ እዚህ ቁ7 ላይም የሚነግረን ሲሆን፤ በተጨማሪ ግን በብዙ ሥፍራ የማናየውን ሁለት በእግዚአብሄር ነጻ የወጡ ነገሥታት ይነግረናል፤ እነዚህም ፍልስጤም ከዮቶርና፣ ሶርያውያን ደግሞ ከቂር ነጻ እንደወጡ ይነግረናል። እግዚአብሄር ሐጥያተኛ በሆኑ መንግሥታት ላይ ዓይኖቹን ለመልካም ሳይሆን ለክፉ እንደሚያደርግ ሲናገር፤ እስራኤልንም እንደማንኛውም መንግሥት ሃጥያተኛ ሆነው ሲገኙና መመለስ እንቢ ሲሉ ዓይኖቹን ማለትም ለክፉ በእነርሱ ላይ እንደሚያደር መናገሩ በፍርዱ እንደማያዳላ እናያለን።
6. እነዚህ ሁለት ቁጥሮች ሁለት የተለያዩ ሃሳቦች ላይ በማተኮር እንደተነገሩ ነው የማየው፤ ይህንንም ስል፤ ቁ9 ትኩረት በመስጠት የሚናገረበት ሃሳብ የእግዚአብሄርን ፍርድ በማጉላት ሲሆን፤ ቁ8 ላይ የተነገረው ሃሳብ ደግሞ እግዚአብሄር አምላክ በፍርዱም ውስጥ እንኳን ምህረትን የሚያሳይ አምላክ እንደሆነና ለእስራኤል ቅሬታን እንደሚያስቀርለት ነው ትኩረቱ። እነዚህ እግዚአብሄር ከሕዝቡ መሃል ለይቶ ሊቀጣቸው ያሰባቸው በቁ10 ላይ የምናገኛቸው ሰዎች "ክፉ አያገኘንም፤ ወይም ዐይደርስብንም የሚሉ ሐጥያተኞች" በማለት የሚገልጻቸው ናቸው።
7. ከፊት ለፊታቸው ስላለው ዘመንና እግዚአብሄር ሊባርካቸው ስላለው በረከት በቁ13 ላይ እግዚአብሄር የሚናገረው ሃሳብ፤ "እነሆ ዓጫጁ ዓጭዶ ሳይጨርስ ዓራሹ በላዩ የሚደርስበት፣ ችግኝ ተካዩም ገና ተክሎ ሳይጨርስ ወይን ጨማቂው የሚደርስበት ጊዜ ይመጣል…" በማለት ይናገራል። በቁ14-15 ውስጥ ነብዩ አሞጽ ከረጅም ጊዜ በፊት ከተናገራቸው የትንቢት ቃሎች መሃል ተፈጻሚነትን እንዳገኙ ከምናውቃቸው መሃል፤ የእስራኤል ሕዝብ መሰደድ፣ የተሰደደው ሕዝብ ወደ ምድሩ መመለስ፣ የከተሞቻቸው መፈራረስ፣ የፈራረሱት ከተሞች መልሰው በመሥራት መኖሪያ ማድረጋቸው፣ ብገዛ ምድራቸው መተከላቸውና የመሳሰሉት ሁሉ ተፈጻሚነትን አግኝተዋል።
8. እነዚህ የእስራኤል ልጆች እግዚአብሄር በብዙ መንገድ ሊናገራቸውና ከጥፋታቸውም ሁሉ ሊመልሳቸው በሚያደርገው ሙከራ የተለያዩ ነብያቱን በመላክ መልዕክቱን ለማስተላለፍ የወሰዳቸውን እርምጃዎች ሁሉ ሕዝቡና ካሕናቱም ሳይቀሩ ጆሯቸውን በመድፈናቸው ይህ ሊደርስባቸው እንደሆነ ሁሉ፤ እኛም ብንሆን እግዚአብሄር ቃሉን ተምረን የእግዚአብሄርን ማንነት እንድናውቅና እርሱን የመምሰል ህይወት እንድንኖር የሰጠንን እድል ካልተጠቀምንበት፤ ለእኛም ቢሆን ይህ የእግዚአብሄር ቃል በር ምናልባት አንድ ቀን የሚዘጋበትና ፈልገን የማናገኝበት ወቅት ሊመጣ እንደሚችል አስባለሁ።